# ተዘግቶ የነበረው መጋርጃ ሲገለጥ፤ ኑዛዜ ወይም ንስሀ በደርግ ባለስልጣናት አንደበት፤ የድንቢጥ ምስክር አይጥ፤

"ምስክርነት ባባልስልጣናቱ አንደበት" በሚል ርእስ በሻምበል ተስፋዬ ርስቴ በተጻፈ መጽሐፍ ላይ ግምገማ

**ከሻምበል አስተዋይ**

ውጭ አገር የምትገኙ ወገኖች

ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ "ምስክርነት በባለስልጣኖች አንደበት" በሚል ርእስ ስለጻፉት መጽሐፍ የግል አስተያየት (ግምገማ) ካደረኩ ጥቂት ጊዜ ሆኖኛል። ከመጽሐፉ ይዘት ጸሐፊው የወያኔ ድጋፍ ያላቸው ስለመሰለኝ አገር ውስጥ ለሚገኙ የግል ጋዜጦች በመስጠት አስተያየቴ እንዲወጣ ወይም በራዲዮ ለማስነበብ አልደፈርኩም። ምክንያቱም ይህ ጽሁፍ አገር ውስጥ እንኳን አገር ውስጥ እንዲወጣ ለማድረግ ማሰቡ ብቻ እራሴን ለከፍተኛ አደጋ መዳረግ መሆኑን ስለተገነዘብኩ ነው።

ስለጻፍኩት አስተያየት አንድ የቅርብ ወዳጄ ለሆነ ሰው ሚስጢሬን ሳጫውተው በአጋጣሚ ቤተሰቦቹን ለመጠየቅ ወደ አሜሪካን አገር ይሄድ ስለነበር ማስታውሻህን ለማን እንደምሰጥ በእርግጥ ባላውቅም በውጭ አገሮች ለሚገኙ የሬዲዮ ጣቢያዎች ፤ በግል እየታተሙ ለሚውጡ የግል ጋዜጦች ወይም ለኢትዮጵያውያን የኢንተርኔት መድረክ ልኬ በውጭ አገሮች የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ እንዲደርሳቸውና እንዲያነቡት ጥረት እንደሚያደርግ ቃል ገብቶልኝ ጽሁፉን ስጥቼዋለሁ።

ጽሁፉን ስታነቡት የስነ ጽሁፍ ስርአት ያልተከተለ መሆኑን ብታውቁም ቁም ነገሩን ተገንዝባችሁ ጽሁፌን በውጭ የሚኙ ወገኖች እንዲያነቡት እንድታድርጉልኝ በደርግ ስርአት በከንቱ ደማቸው በፈሰሰው ሰማእታት ስም እጠይቃለሁ።

የቀድሞ የደርግ መንግስት አገልጋይ የነበርኩ

ሻምበል አስተዋይ

ለጓድ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ

ከ1983 ዓ.ም. ወዲህ በደርግ ስርአት ስለነበረው የአገር መከላከያ ሚኒስቴር መ/ቤት አንዳንድ መኮንኖች በወቅቱ ስለነበረው የመለዮ ለባሹ ሚናና ምን አይነት አመራር ይሰጥ እንደነበር ገመናቸውን ጭምር በመጽሐፍ መልክ ጽፈው ህብረተሰቡ እንዲያነበው ማድረጋቸው ይታወሳል። በተመሳሳይ በደርግ ስርዓት ስለነበረው የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት የተጻፉ ጽሁፎች እንድነበሩ ሲታውቅ በቅርቡ እርስዎ " ምስክርነት በባለስልጣናቱ አንደበት" በሚል ርእስ መጽሐፍ መጻፍዎንና በመጻሕፍዎ ውስጥ በገጽ 160 እንደገለጹት የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን ታሪክ ማወቅ ይገባዋል ብዬ ስለማምን ይህንኑ ለማሟላት ከኔ የደረሱትን መረጃዎች ጊዜው ይፈቅዳል ብዬ ያመንኩባቸውን ሁሉ አውጥቻለሁ ብለዋል። በመጀመሪያ ሁላችንንም እንኳን ደስ ያለን እላለሁ።

መጽሐፉን በመደጋገም አንብቤዋለሁ። በመጽሐፉ ውስጥ በደርግ ስርዓት በነበረው የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት አማካኝነት ለአገርና ለሕዝብ የሚጠቅሙ ብዙ ተዳናቂና የስለላ ተግባሮች መፈጸሙን፣ ባንጻሩም በአገርና በሕዝብ ላይ ተፈጽመዋል ያልዋቸው ከፍተኛ የአገር ክህደት ወንጀለኞች ናቸው ብለው የገለጿቸውን ፣ እንዲሁም በመከላከያ ሚኒስቴር የተለያዩ ማዕረግ የነበራቸው መኮንኖች ብዛት ያላቸው የበታች ሹሞችና ወታደሮች ለአገራቸው የሚፈለግባቸውን ግዳጅ ከሕይወት መስዋእትነት ጀምሮ ከባድና ቀላል የአካል ጉዳት የደረሰባቸው አባሎች እንደነበሩ አሁንም ከመሞት በላይና ከመኖር በታች ሆነው የሚኖሩ እንዳሉ በተቃራኒው ከአገር ጥቅም በላይ የግላቸውን ጥቅም በማስቀደም በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የክህደት ወንጀል የፈጸሙ መኮንኖች ናቸው ያሏቸውን አንዳንዶቹን በስም ጠቅሰው እንድናውቃቸው አድርገዋል።

<u>ውድ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ</u>

በእርስዎ የቅርብ አለቃዬ በነበሩትና በእኔ መሐል በእውቀት፣ በሥራ ልምድ፣ በማዕረግ መመጣጠን አለመኖሩን እረዳለሁ። እርስዎ በመደበኛ እጩ መኮንንነት ተቀጥረው በኢትዮጵያ ፖሊስ ኮሌጅ ውስጥ ይሰጥ የነበረውን የፖሊሲና የአካዳሚክ ትምህርት ለሶስት አመት ተምረው በመኮንንነት የተመረቁ ሲሆን፤ እኔ በፖሊስ ሠራዊት ውስጥ በተራ ወታደርነት ተቀጥሬ ከብዙ ዓመት አገልግሎት በኋላ ለበታች ሹሞች ይሰጥ የነበረውን የሙያ ፈተና አልፌና በፖሊስ ኮሌጅ ውስጥ ይሰጥ የነበረውን የአጭር ጊዜ የሙያ ትምህርት ተከታትዬ በመኮንንነት ተመርቄአለሁ።

እርስዎ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ገብተውና ተምረው በሕግ የባችለር ዲግሪ ሲያገኙ እኔም እንደ አቅሚቷ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በማታው የትምህርት ክፍለ ጊዜ በአማርኛ ይሰጥ የነበረውን የሕግ ትምህርት ተምሬ በዲፕሎም ተመርቄያለሁ።

እርስዎ ወደ ቀድሞው ሶቪየት ሕብረት ተልከው ከፍተኛ የመረጃ ትምህርት ተምረው እንደተለመደው ከፖሊስ ሠራዊት ወደአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት ማዕከላዊ ምርመራ ድርጅት ተዛውረው እንዲሠሩ ሲደረግ እኔም አገር ውስጥ በሚገኘው የመረጃ ትምህርት ማዕከል ተልኬ በመረጃ የሙያ ትምህርት ከተከታተልኩ በኋላ ማዕከላዊ ምርመራ ድርጅት ተመድቤ የደርግ ሥርአት እስከወደቀ ድረስ በመርማሪነት ሳገለግል ቆይቻለሁ።

እርስዎ ማዕከላዊ ምርመራ ድርጅት ውስጥ በመምሪያ ኃላፊነት የእኛ የመርማሪዎች ኃላፊና ተቆጣጣሪ አልፎም ምርመራዎችን በማጠናከር የሚያረጋግጡ የነበሩ መሆኑ ግልጽ ሲሆን እኔም በመርማሪነት የረጅም ዓመት የስራ ልምድ ያካበትኩ በመሆኔ እርስዎ አለቃዬ በጻፉት መጽሐፍ ላይ ግምገማ መሰል ጽሁፍ ባቀርብ ቅር እንደማይሰኙ እምነቴ የፀና ነው።

<u>ውድ አንባቢዎች</u>

ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ ስለአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት ሲጽፉ በተለያዩ ገጾች የሚኒስትሩ መ/ቤትንና በስሩ የነበሩት ልዩ ልዩ ድርጅቶችና ክፍሎች አጠራር የተለያዩ ስሞችን እየሰጡ ስለጻፏቸው ለአንባቢዎች ግልጽ እንዲሆን በማለት የቀድሞውንና በደርግ ስርአት ይጠሩበት የነበሩትን ስሞች በመለየት እንደሚከተለው ለመግለጽ እሞክራለሁ።

- ከ1966 ዓ.ም. በፊት አገር ግዛት ሚኒስቴር ተብሎ ይጠራ የነበረው በደርግ ስርአት አገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር
- ልዩ ካቢኔ ተብሎ ይጠራ የነበረው ድርጅት ውጭ አገሮች ጥናትና ምርምር ድርጅት
- የፖሊስ ሠራዊት ተብሎ ይጠራ የነበረው የአብዮታዊ ፖሊስ ሠራዊት
- የሕዝብ ፀጥታና ጥበቃ ተብሎ ይጠራ የነበረው የውስጥ ደህነነት
- በፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ አዛዥ ስር ይመራ የነበረውና የልዩ ቅርንጫፍ ተብሎ ይጠራ የነበረው መምሪያ ለተወሰኑ ጊዜያት የውንብድና መቆጣጠሪያና መከላከያ በመጨረሻም ማዕከላዊ ምርመራ ድርጅት ተብሎ እንዲጠራና ተጠሪነቱም በቀጥታ ለአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር እንዲሆን ተወስኗል።

ይህ የአቋም ለውጥ የተደረገበት ዋናው ምክንያት የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሩ በቀጥታ ለመቆጣጠርና ለማዘዝ እንዲያስችላቸው ነበር።

<u>ውድ አንባቢዎች</u>

"ምስክርነት በባልስልጣናቱ አንደበት" በሚለው መጽሐፍ ላይ ላደረግኩት ግምገማ " ተዘግቶ የነበረው መጋረጃ ሲገለጥ" የሚል ርእስ የሰጠሁበት ዋናው ምክንያት እነ ሻምበል አምሃ አበበና የመሳሰሉት በመቶዎች የሚቆጠሩ ብዙ ወጣት መኮንኖች የበታች ሹሞችና ወታደሮች በኮርስ ወይም በቅርብ ጓደኞቻቸው የሀሰት ጥቆማ ተካሂዶባቸው ህይወታቸው የተቀጨበት ፤ አካለ ስንኩላን የሆኑበት ምክንያት ብዙ ሚስጢር መውጣት በመጀመሩ ነው።

ወደ መጽሀፉ ይዘት ከመግባቴ በፊት ግን ኮሎኔል መርሻ ወዳጆና አምባሳደር (አቶ) ሞገስ ሀ/ማርያም በመጽሐፉ ጀርባ ላይ የሰጡት አስተያየት የድንቢጥ ምስክር አይጥ ሆኖ ስላገኘሁት ጥቂት ነገሮችን ማለት እፈልጋለሁ።

ኮሎኔል መርሻ ወዳጆ በመጽሐፉ ሽፋን ላይ ስለመጽሐፉ የሚከተለውን አስተያየት ሰጥተዋል። " መጽሐፉ ከእውነተኛ ምንጭ የፈለቀ በመሆኑ የደርግን አመራር ጊዜ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ መጽሐፍ ነው" ብለዋል። ኮሎኔል መርሻ ወዳጆ ለብዙ ዓመታት ፖሊስ ኮሌጅ ውስጥ በመምህርነት ያስተምሩ እንደነበር እኔንም ጀምሮ በእጩ መኮንነት በምሰለጥንበት ወቅት ያስተምሩኝ ስለነበር ትልቅ አክብሮት አለኝ ።

ሆኖም በሰጡት አስተያየት ምንም እንኳ መጽሐፉ በርካታ ከእውነት የራቁ አሉባልታዎችን ያካተተ ሆኖ ሳለ ከእውነተኛ ምንጭ የሚለው አነጋገራቸው እውነተኛነቱን የማያመለክት ቢሆንም መጽሐፉ የደርግን አመራር ጊዜ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው ማለታቸው ግን እውነትን ተናግሮ ከመሸበት ማደር የሚለውን ይትበሃል አስታውሶኛልና በግሌ አመሰግናቸዋለሁ።

አምባሳደር ሞገስ ሀ/ማርያም ደግሞ የሚከተለውን አስተያየት ሰጥተዋል። " ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ የደርግ መንግሥት ታሪክ ለመከተብ በየትኛውም ቦታ ቢሆን የማይገኘውን እድል ተጠቅመውበታል። በተጨማሪም የተለያዩ መጽሐፍትን አንብቦ በዋቢነት አጣቅሷል። በሶስተኛ ደረጃ በስራ ምክንያት ሁኔታዎችን ለመገንዘብ ስለተቻለ የተሟላ ዝግጅት ሆኖለታል። እናም ይህ ታሪክ ተዝቆ የማያልቅን የወርቅ ማእድን ይመስላል" ብለዋል። ውድ አንባቢዎች - አምባሰደር ሞገስ ሀ/ማርያምን በሚመለከት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አባል ሆነው እንዴት አስተያየት ሊሰጡ እንደቻሉ ግር ብሎኝ ነበር። በአስተያየታቸው ውስጥ ተስፋየ ርስቴን በአንድ መ/ቤት ስንሠራ አውቀዋለሁ በማለታቸው ስለ ማንነታቸው ለማወቅ ጉጉት አድሮብኝ በአደረጉት የመረጃ ግኝት በቀ.ኃ.ሥ. የዘውድ አገዛዝ ጊዜ ልዩ ካቢኔ በኋላም ውጭ አገሮች ጥናትና ምርምር ተብሎ ይጠራ ከነበረው ድርጅት ውስጥ ያሳዩት በነበረው የሥራ ትጋትና ችሎታ እስከ ም/ሚኒስቴርነት ማዕረግ የደረሱ በመጨረሻም አድርገውት ለነበረው ከፍተኛ አስተዋጽኦ በአምሳደርነት ተሹመው ውጭ አገር ሄደው በማገልገል ላይ እያሉ የደርግ ስርአት በመገርሰሱ በአሁኑ ጊዜ የት እንዳሉ ባላውቅም ከኢትዮጵያ ውጭ እንደሚኖሩ ተረድቻለሁ።

አምባሳደር ሞገስ የደርግን አስከፊና አሳፋሪ ታሪክ ተዝቆ የማያልቅ የወርቅ ማዕድን ከማለት ይልቅ በአገራችን የደርግ ስርአት ከተመሰረተ ጀምሮ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን መለዮ ለባሾች፤ ወዛደሮች፤ ገበሬዎች፤ ምሁራኖችና ወጣቶች በየመንደሩ በአውራ መንገዶችና በተለያዩ ስውር ቦታዎች ያለአንዳች ማስረጃና ፍርድ ፀረ ደርግ፤ ፀረ አንድነት ወዘተ.... በሚል የተጨፈጨፉና በየቦታው የተጣሉ ኢትዮጵያውያንን የሚያስታውስ ተለቅሞ የማያልቅ የሰማእታት የአጽም ክምር ቢሉት የተሻለ ነበር እላለሁ።

አንባቢያንን ላለማስልቸት በቀጥታ ወደ መጽሐፉ ግምገማ አልፋለሁ።

1. <u>የጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም አሟሟትን በሚመለከት</u>

ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ ጄኔራል ሚካኤል አንዶምን በሚመለከት እንዲህ ብለዋል። " ጄኔራል አማን የጦር አለቆችን ማነጋገር መጀመራቸው የደርግ አባላቱ ሲረዱ የፍርሃትና የጭንቀት ብርድ ውስጥ ከተታቸው። ለአራተኛ ጊዜ ጄኔራል ግዛው በላይነህ በብዙ ጥረት በስልክ አግኝተው ሲያነጋግሯቸው ግዛው ' አገራችን በእነዚህ ቂጣቸውን ባልጠረጉ ጨምላቆች ተመርታ ወደ ጥፋት መሄድ የለባትም፤ አንተም ሠራዊትህን አዘጋጅና ይልቅ ተነሳ አሉ። ታዲያ ጄኔራል ግዛው በላይነህ ጄኔራል አማንን ይተዉ እንጂ እርስዎን ከዚህ ታላቅ ቦታ ያስቀመጥዎት እኮ እነዚህ ቂጣቸውን ያልጠረጉ ያሏቸው ናቸው። እባክዎን ትእግስት ያድርጉና ተባብረን ለአገር የሚበጅ ነገር እንስራ በማለት ለመሸምገል ሞክረው ሳይሳካላቸው ቀረ። ጄኔራል አማንና ጄኔራል ግዛው ያደረጉት የስልክ ንግግር ከደህንነቱ ተጠልፎ በደህንነቱ ቢሮ አማካኝነት ለሻለቃ መንግስቱ ደረሰ። ይህ በሁለቱ ጄኔራሎች መሀል የተደረገ የስልክ ልውውጥ ጄኔራል ግዛው በላይነህ በደርግ እስከመጨረሻው የተከበሩ እንዲሆኑ የጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም መጨረሻ ቅጽበታዊ እንዲሆን የፖለቲካ ሁኔታው አስገደደ" (ገጽ 56) " ይህን መልእክት የጠለፈው ልዩ ካቢኔ በወታደራዊ አስተዳደር

ወቅት የውጭ አገሮች ጥናትና ምርምር ድርጅት የሚባለው የውጭ መረጃ (Positive Intelligence) ቢሮ ነው" (ገጽ 155) ይላል.

***አስተያየት***

ውድ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ፦ ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም በ1967 መጀመሪያ ወራት የአገሪቱ ርዕሰ ብሔር በሆኑ በጥቂት ወራት ውስጥ የደርግ አባላቱ አገርን ለመምራት ብቃት እንደሌላቸው አገሪቱም በነሱ ተመርታ ወደጥፋት መሄድ የለባትም ማለታቸው አገራችን አሁን ከደረሰችበት እውነታ ጋር ሲመዛዘን ትክክለኛ ትንበያ የተናገሩ አይመስልምን?

ሻለቃ መንግስቱ ኃይለማርያም በህይወት ከሌሉት ከኮሎኔል ዳንኤል አስፋውና ከጥቂት የደርግ አባሎች ጋር ብቻ ተመሳጥረው ጄኔራል አማን እንዲገደሉ ያስደርጋሉ። በማከታተልም በፈፀሙት አስደንጋጭ እርምጃ በደመነፍስና በመደናበር ይመስላል ወይም አጥፍቶ መጥፋት ከሚለው ምሳሌ ጋር በሚመሳሰል መልኩ በቀ.ኃ.ሥ. ስርአት ሚኒስትሮች፤ ም/ሚኒስትሮች፤ በተለያዩ የመንግስት መዋቅር ውስጥ በኃላፊነት ያገለግሉ በነበሩ የሲቪልና ከፍተኛ የወታደራዊ እውቀትና ልምድ በነበራቸ ጄኔራሎችና ከፍተኛ መኮንኖች ላይ ያለፍርድ እንዲረሸኑ ማድረጋቸው ሻለቃ መንግሥቱና አብዛኞቹ የደርግ አባላት አገርን ያህል ለመምራት ብቃት የሌላቸው ናቸው ከማለትም በላይ በአእምሮ ሕመም የተለከፉ አይነት ፍጡሮች አይመስሉዎትምን?

ጄኔራል አማን ሚካኤል አንዶም የደርግን ስርአት ለመቀየር የነበረው እቅዳቸው ሊከሽፍ የቻለው በአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር የውጭ አገሮች ጥናትና ምርምር ተብሎ ይጠራ የነበረው ድርጅት ስልክ በመጥለፍ ባስተላለፈው ሪፖርት መሠረት መሆኑን ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ ልብ ሊሉት ይገባል እላለሁ።

2. <u>የግንቦት 8 1981 የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራን በሚመለከት</u>

የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራውን አስመልክቶ እንዲህ ብለዋል። " የሆስፒታል ሴራ ፦ የመፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ ሴራ ሲያራምዱ የነበሩ ከፍተኛ መኮንኖች በ1979 ዓ.ም. ሁለተኛ መንፈቅ አንዱ አጋማሽ ጦር ኃይሎች ሆስፒታል ለህክምና ገብተው ተኙ። አላማቸውን ዳር ለማድረስ በህክምና ሰበካ ሆስፒታል ውስጥ ጄኔራል መርዕድ ፤ ተካልኝ ንጉሤ በዋናነት የሚጠቅሱ ሲሆን ሌሎች ደግሞ እነዚህን ታካሚ መኮንኖች ለመጠየቅ ወደሆስፒታሉ እየገቡ አላማቸውን ከግቡ ለማድረስ ጥረት አድርገዋል። በታካሚነት ሽፋን ሆስፒታል ውስጥ ሲሰባሰቡ መንግስትም የራሱን ታማኝ ባለሥልጣናት በህመም ሽፋን እንዲተኙ አድርጎ የከፍተኛ ጄኔራሎችን እንቅስቃሴ ይከታተል ነበር። ከፍተኛ ጄኔራሎች ከተኙበት ክፍሎች ከተቀበሩ የኤሌትሮኒክስ መሣሪያዎችና ስልኮችን በመጠቀም ያደረጉትን ንግግርና የሰጡትን መመሪያ በቴክኒክ የመረጃ አሰባሰብ ስልት የኢንተለጀንሱ ስብስብ ተጧጡፎ እንደነበር የኢንተለጀንሱ ቢሮ ሚኒስትር አረጋግጠዋል።"

"ደህንነቱ ልዩ ልዩ ባለሙያዎች በክትትል፣ በስልክና ፖስታ በመጥለፍ ቢሮዎች ውስጥ ልዩ ልዩ ዘመናዊ የስለላ መሣሪዎችን በማስቀመጥ የመፈንቅለ መንግሥቱ ግልበጣ አመጽ ተባባሪ በመሆን ሚስጢር ያሾልኩ ከነበሩ መኮንኖች ያገኘው ከነበርው ኢንተለጀንስ በተጨማሪ ነው።" (ገጽ 183-184)

<u>አስተያየት</u>

በ1966 ዓ.ም. ተቀጣጥሎ ለነበረው ሕዝባዊ አመጽና አብዮት የመለዮ ለባሹ ክፍል የተወሰነ አስተዋጽኦ ማድረጉ ሐቅ ነው።

በወቅቱ የአገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤትን በሰው ኃይል ለማጠናከር በሚል አብዛኞዎቻችን ከልዩ ልዩ የጦር ክፍሎችና ከፖሊስ ሠራዊት ተዛውረን የመጣን ሲሆን ከመሥሪያ ቤቴ የሰው ኃይል ሲነፃፀር ብዛት ባይኖራቸውም በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች በዶክትሬት፣ በማስትሬት፣ በባችለር ዲግሪ ከዚያም ዝቅ ሲል በዲፕሎማ የተመረቁ በተጨማሪ ብዛት ያላቸው ሠራተኞች ወደ ተለያዩ ሶሻሊስት አገሮች ተልከው የመረጃና የሶሻሊስት ርእዮተ ዓለም ትምህርት የተከታተሉ አባሎች እንደነበሩ ከዚያም በላይ የብዙ አመት የሥራ ልምድ ያካበቱ ሠራተኞች እንደነበሩ ሐቅ ነው።

ከ1966 ዓ.ም. እስከ 1980 ዓ.ም. ድረስ በነበረው ጊዜ መለዮ ለባሹ (ደርግ) የመንግስቱን የአመራር ስልጣን ይዞ እንዲቆይ አብዮቱን በመንከባከብ ሽፋን የብዙ ኢትዮጵያውያን ደም በከንቱ ምፍሰሱን አገሪቷም ኬድገት ይልቅ እየቆረቆዘች መሄዷን በሁልንተናዊ መልኩ ችግር ውስጥ እንደገባች አገሩቷም የመገነጣጠል እድል ሊገጥማት እንደሚችል ጥቂት የደህንነቱ አባሎች የተረዱና ስጋት ያደረባቸው አባሎች እንደነበሩ እሙን ነው። አብዛኞቻችን ግን በቂ ግንዛቤ እንዳልነበረን ሳስታውስ ሀፍረት ይሰማኛል። ሆኖም በመሥሪያ በቱ ውስጥ በቁልፍ ቦታዎችና በአመራሩ ቁንጮ ላይ የነበሩ አለቆቻችን ከአለፈው ስህቶቻቸው ተምረው እንዲሁም የነጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ ፣ የእነ ጄኔራል ጽጌ ዱቡና የእነ ከኮሎኔል ወርቅነህ ገበየሁና መሰሎቻቸውን አርአያ ተከትለው የሕዝቡም እሮሮ ተሰምቷቸው በግንቦት 8 ቀን 1981 ዓ.ም. በጄኔራል መርዕድ ንጉሤ፣ በጄኔራል ፋንታ በላይና መሰሎቻቸው የደርግን ሥርዐት ለመቀየር አድርገውት ለነበረው ሙከራ ግቡን እንዲመታ ከማድርግ ይልቅ እንዲከሽፍ ለማድረግ ከፈተኛውን ሚና ተጫውቷል። በውጤቱም ብዙ የወታደር ሙያ እውቀት ልምድ ችሎታ የነራቸው መኮንኖቻችንን አጥተናል። በሰሜን በኩል የነበረው የኢትዮጵያ ጦር መፈረካከስና መበተን የጀመረው ከግንቦት 8 ቀን 1981 በኋላ እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህም ሊሆን የቻለው ከራስ ወዳድነት ከአገሪቱ አጠቃላይ ጥቅም ይልቅ የጥቂት የደርግ አባሎችንና የራሳቸውንንም ጥቅም ለማስጠበቅ ከነበራቸው ጉጉት ጥቂቶቹ ደግሞ ካለፉት ብዙ ዓመታት ጀምሮ የምዕራባውያን አገሮች ቅጥረኞች ስለነበሩ ዋና ተልእኮዋቸው ሕዝባውያን አብዮት ከማሰቀልበስ በቀር ሌላ አማራጭ ስላልነበራቸው ሆን ተብሎ የተፈጸመ ፀረ ሕዝብ ድርጊት ነው የሚሉ ብዙ ሰዎች ይናገራሉ። ለዚህም ዋና ማረጋግጫው ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ በፃፉት መጽሐፍ ውስጥ ተቀንጭበው የተጻፉት በቂ መረጃዎች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ በአቶ ግርማ ዋቅጅራ ይመራ የነበረው ልዩ አቃቤ ሕግ በእነ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ላይ የቀረበው ክስና የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን (ብይን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ የተሟላ ነው ባይባልም በደርግ ሥርዐት ተፈጽመው ነበር ስለተባሉት ወንጀለኞች የሚያብራራ ስለሆነ አንባቢዎች ጥራዙን ፈልጋችሁ ማንበቡ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው የሚል እምነት አለኝ።

3. <u>ቀድሞ ስሙ ልዩ ካቢኔ በደርግ ሥርዓት ውጭ አገሮች ጥናትና ምርምር ተብሎ ይጠራ የነበረውን ድርጅት በሚመለከት፤</u>

ይህን ድርጅት አስመልክቶ ፀሐፊው እንዲህ ብለዋል። " የኢትዮጵያ የውጭ መረጃ ድርጅት ሠራተኞች ከጂቡቲ ሆነው በወኪሎቻቸው የሱማሌን የጦር ቢሮ ቦርቡረው ምስጢር ቃርመዋል። የኢትዮጵያ አየር ኃይል ኢላማውን አስተካክሎ መምታት የተሳካላትም የመረጃው ድርጅት ባቀረበለት መረጃዎች መሠረት ውጊያዎችን (Operations) በመንደፍ ነበር። የሱማሊያ ሚስጢር በመስኮብ አማካሪዎች ተገኘ የሚሉ ሰዎች አሉ። መገኘቱ ባይታበልም ዋናው ምንጭ ግን የራሳችን የኢትዮጵያ የውጭ መረጃ ቢሮ ነበር። የድህነቱ መሥሪያ ቤት ውስጥ ምክትል ሚኒስቴር የነበሩት ባለሥልጣን ይህን አስመልክቶ የኢትዮጵያ አየር ኃይል መሥሪያ ቤት ተደጋጋሚ ምስጋና ያቀረበላቸው መሆኑን ይናገራሉ።" ብለዋል።

<u>አስተያየት</u>

በእርግጥም የውጭ መረጃ ሠራተኞች ጂቡቲ ሆነው የሱማሌን መንግሥት የጦር ቢሮ ቦርቡረው ውጤት አስገኝተዋል የሚለው እውነትነት ካለው ሁላችንንም ማለትም በደህነነት መ/ቤት ውስጥ የነበርነውን ሠራተኞች ሁሉ የሚያኮራን ነው።

ከ 1960 ዓ.ም. መጀመሪያ ዓመታት ጀምሮ ኤርትራን ለማስገንጠል የጀብሃና የሻዕቢያ ቡድን አባሎች በኋላም ከ 1966 ዓ.ም. ወዲህ የሻዕቢያና የ ወያኔ ቡድን አባሎች በጋራና በተናጠል አገር ውስጥ በስውር ይንቀሳቀሱ እንደነበር በተመሳሳይ ጂቡቲ ኬኒያ ሱማሌና በተለይም ሱዳን ውስጥ ጽሕፈት ቤቶቻቸውን ከፍተው በከፍተኛ ደረጃ ፀረ ኢትዮጵያ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ እንደነበር ይታወቃል። በተጨማሪም በተለይም ከኤርትራ አዋሳኝ በሆኑ የሱዳን ከተሞችና መንደሮች ውስጥ ቁሳቁሶችን፣ ቀለቦቻቸውን፣ ልዩ ልዩ ከባድና ቀላል የሆኑ የጦር መሣሪያዎችን ያከማቹ የነበር ግዙፍ የሆኑ መጋዘኖች እንደነበሯቸው። ያከማቿቸው ንብረቶችና የጦር መሳሪያዎች በነበራቸው ከባድና መለስተኛ በሆኑ የጭነት ተሽከርካሪዎቻቸው ወደሰሜኑ የኢትዮጵያ ጠረፍ ከተሞች ከዚያም ሠራዊቶቻቸው ይገኙበት ወደነበሩ ልዩ ልዩ ቦታዎች አሰርገው ያስገቡ እንደነበር በገሃድ ይፋ እየሆነ ይነገራል። ምነው ታዲያ የኢትዮጵያ የውጭ መረጃ ቢሮ ሠራተኞች አገር ውስጥ በስውር ይንቀሳቀሱ የነበሩትን የሻዕቢያና የወያኔ አባሎች ግንኙነታቸውን ስልክ በመጥለፍ እንዲያዙ ወይም እንቅስቃሴያቸው እንዲገታ አላደረጉም። ምነው ጂቡቲ ውስጥ ፈጽመነዋል እንደሚሉት የሻዕቢያና የወያኔ ቢሮዎችና ጽሕፈት ቤቶቻቸውን ቦርቡረውና እንቅስቃሴዎቻቸው እንዲገታ አላደረጉም። ምነው በኢትዮጵያ ጠረፎች አካባቢ ነበሩ የተባሉትን መጋዘኖቻቸው ተሽከርካሪዎቻቸውን የሚወድምበትን እቅዶች በመንደፍ ለኢትዮጵያ አየር ኃይልም ሆነ ተመሳሳይ ግዳጅ ለመፈጸም ብቃትና ችሎታ ለነበራቸው( አየር ወለድ) ይባሉ ለነበሩ የጦር ክፍሎች መረጃው እንዲረጋገጥ አልተደረገም ወይስ የውጭ መረጃ ድርጅት ሠራተኞች ሻዕቢያንና ወያኔን እንዳይከታተሉ ማዕቀብ ተጥሎባቸው ይሆን? ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ በጻፉት መጽሐፍ በገጽ 141 የውጭ አገሮች ጥናትና ምርምር ድርጅት ተወካይ ከአሜሪካን ከእስራኤልና ከምዕራብ ጀርመን የመረጃ ተወካዮች ጋር ውጭ አገሮች ጥናትና ምርምር ድርጅት ውስጥ እየተገናኙ ውይይት ያደርጉ እንደነበር ገልጸዋል።

ወያኔና ሻዕቢያ ይመለከቱ የነበሩ መረጃዎች ይፋ እንዳይወጣና እርምጃ እንዳይወሰድባቸው አፍነው የሚያስቀሩ ኃይል ነበርን? ወይስ ሕዝባዊ ለውጥና እንቅስቃሴ ግቡን እንዳይመታ ደህንነት መ/ቤት ውስጥ በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የነበሩ ግለሰቦች ቡድኖች ነበሩ? የተቀረውን ግንዛቤና አስተያየት ለአንባቢዎች እተዋለሁ።

በገጽ 141 ላይ ፀሐፊው ስለውጭ መረጃ ብሮ የሚከተለውን ጽፈዋል።
" የውጭ መረጃ ቢሮ ብዙ ቁም ነገሮችን ሠርቷል። እርሳቸው ፕሬዚዳንቱም የመረጃውን ጥንካሬ አልካዱትም። የኢትዮጵያ መረጃ ቢሮ አብክሮ ሁኔታዎችን ተገንዝቦ ለፕሬዚዳንቱ አሳውቋል። ፕሬዚዳንቱ አውቀው ስምምነታቸውን በመግለጻቸው ከአሜሪካው ሲ. አይ. ኤ. ተወካይ፤ ከእስራኤል ሞሳድ ተወካይና ከምዕራብ ጀርመን መረጃ ድርጅት ተወካይ ጋር ግንኙነት እንዲደረግ ተፈቅዷል። በዚህ የተነሳ የነዚህ አገሮች የመረጃ ተወካዮች ከኢትዮጵያ የውጭ መረጃ ቢሮ ተወካይ ጋር ውጭ አገሮች ጥናትና ምርመር ድርጅት ውስጥ እየተገናኙ ብዙ ውይይቶች አድርገዋል። የውይይቶችም ጭብጥ ለፕሬዚዳንት መንግሥቱ በመረጃው ቢሮ የበላይ ባልሥልጣን አማካኝነት ደርሰዋል። ከዚህ በመነሳት የእስራኤል የደህነነት (የሞሳድ) ባለሥልጣን በኋላ በኢትዮጵያ አምባሳደር የሆነው በመረጃ ትምህርት ማዕከል ውስጥ እንዲኖር ተድርጎ ነበር። ፕሬዚዳንቱ ፈቃድ በመስጠታቸው ሁለት ጊዜ የኢትዮጵያ መረጃ ቢሮ ልዑካን ወደ እስራኤል ሄደዋል።"

<u>አስተያየት</u>

በ 1966 ዓ.ም. መጨረሻ ወራት ጀምሮ ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ከጥቂት የደርግ አባሎች ጋር በመሆን ለምዕራባውያን አገሮች ቅጥረኞች በነበሩ ምሁራን እየታጀቡ ምክርም እየተለገሳቸው አገር ወዳዱ፣ ኮሚኒስቱ፣ ቆራጡ፣ መሪያችን ሲባሉ እውነት እየመሰላቸው ለአገራቸው ተቆርቋሪ የነበሩ ብብዙ ሺ የሚቆጠሩ ተራማጅ ምሁራንን ወጣቶችን ሥልጣኔን ይቀናቀኑኛል ብለው የሚጠረጥሯቸውን መለዮ ለባሾችን ጭምር ሥልጣናችውን እስከሚለቁ በት ጊዜያት ያስጨፈጭፉ እንደነብር ይታወቃል። በመጨረሻም በየካቲት ወር 1983 ዓ.ም. ገደማ ፕሬዚዳንት መንግሥቱ በሥልጣን ዘመናቸው ብዙ ከፍተኛና ዘግናኝ የሆኑ ወንጀሎችን ስለፈጸሙ ድርጊታቸውም ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ሊያስቀርባቸው እንደሚችል አገሪቷም የእርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ልትገባ እንደምትችል ከፍተኛ ስጋት እንዳደረባቸው ቢሮዎቻቸውን ውጭ አገር ጥናትና ምርምር ውስጥ አድርገው የነበሩት ፕሬዚዳንት መንግሥቱን የሚመለከት ብዙ የውጭ መረጃ ቢሮ ብዙ ቁም ነገሮች ሠርቷል። የአሜሪካን፤ የእስራኤልና የምዕራብ ጀርመን መንግሥት የመረጃ አማካሪዎች በፕሬዚዳንቱ ዙሪያ በነበሩ የቅርብ ሰዎች አማካኝነት ፕሬዝዳንት መንግሥቱ እንዲያውቁት ያደርጋሉ በተከታታይም ከላይ የተገለጹት የውጭ አገሮች የመረጃ ሰዎች በአገሪቱ ውስጥ የርስ በርስ ጦርነት እንዳያስከትል እንደ አማራጭ መፍትሔ ነው ብለው አቅርበዋቸው ከነበሩት መሐል

- የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) ሌሎች የተቃዋሚ ፓርቲዎች በሙሉ የሚሳተፉትበት ጊዜያዊ የሽሽግር መንግሥት እንዲመሠረት እንድሚያደርጉ፤

- ፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃ/ማርያም ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው እንዲለቁና ለዚህም በሳቸውም ሆነ በመላ ቤተሰቦቻቸው ላይ ምንም አይነት ጉዳት ሳይደርስባቸው ወደፈለጉበት አገር እንዲሄዱ እንዲያመቻቹላቸው፤
- በስደት በሚኖሩበት አገር የኑሮ ችግር እንዳይገጥማቸው ለህይወት ዘመናቸው የሚሆን በቂ የሆነ በርካታ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እንደሚሰጣቸው ቃል የተገባላቸው ሲሆን ፕሬዚዳንት መንግሥቱ በሥልጣን ላይ እያሉ በተለያዩ ሥፍራዎች ንግግር አድርገው ማሳረጊያቸው ኢምፔሪያሊዝም ፣ ካፒታሊዝም፣ ፊውዳሊዝም፣ ይወድማሉ ፤ አንድ ጥይት እስኪቀረኝ ለኢትዮጵያ እስከሞት እታገላለሁ እያሉ ይፎክሩ እንዳልነበር አለምንም ማንገራገር ጥቂቶቹን የወንጀል ተባባሪዎቻቸውንና አጋሮቻቸውን እንኳን ሳያስከትሉ ሹልክ ብለው ፈርጥጠው ከአገር መውጣታቸው ሠምተንና አይተን ታዝበናል። ስለዚህ የፕሬዚዳንት መንግሥቱ ኃ/ማርያም ማንነትና የሚስጥር አማካሪዎቻቸው እነማን እንደነበሩ ከላይ የተገለጸው ጥሩ ማስረጃ ነው እላለሁ። ለማጠቃለል ከላይ የተገለፀው አይነት ድርጊት ብዙም ሳይቆይ ጠቅላይ ሚኒስትራችን መለሰ ዜናዊ ይፈጽሙታል የሚል እምነት ስላለኝ የወያኔ የሲቪልና የጦር ባልሥልጣኖች እንደደርግ ባልሥልጣኖች በእስር ከመማቀቅ ወይም የከፉ ሁኔታዎች ይግጥማቸው ይሆናል የሚል ስጋት ስላለኝ አሁኑኑ ከሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ለመታረቅ እኚሁን አገር አጥፊ የሆኑትን አምባገነን መሪና ጥቂት አጫፋሪዎቻቸውን የሚወገዱበትን መንገድ አንድትሹ በዚህ አጋጣሚ ላሳስባችሁና የግሌን ምክር አለግሳለሁ።
-

4. <u>ሻምበል አመሃ አበበን በሚመለከት</u>

ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ ሻምበል አመሃ አበበን በሚመለከት እንዲህ ብለዋል።
" በጥር ወር መጀመሪያ 1969 ዓ.ም. ሻምበል አመሃ አበበ መንግሥተ አብ ባህሩና ቁምላቸው ተካ ማይጨው አደባባይ አጠገብ ከምትገኘው ሜክሲኮ ባር ቡና ሲጠጡ ፀሐፊው አግኝቷቸዋል። (ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ ራሳቸውን ማለታቸው ነው) ሶስቱም መኮንኖች የኮርስ ጓደኞች ስለሆኑ አብሯቸው በመቀመጥ ሻይ ሲጋበዝ አመሃና መንግሥተ አብ ስለመንግሥቱ ኃይለ ማርያም በሥልጣን መቀረፍ ይወያዩ ስለነበር ለማዳመጥ በቅቷል። በዚህ ዕለት አመሃ አበበ ከአሁን በኋላ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ብቻውን ጦር አያንቀሳቅስም፣ ፋይናንስ አያንቀሳቅስም፣ የርሱ ሥልጣን አብቅቷል። በማለት ለሶስታችን ነገረን። ፀሐፊው ለመሆኑ ዳንኤል አስፋው ከሻለቃው አጠገብ እንዳለ ነው ወይስ ተቀይሯል ስል ጠይቄው አመሃ ዳንኤልን ተወው በማለቱ አትሳሳቱ ብዬው ነበር።
ከ 15 ቀን በኋላ መ/አ አለማየሁ ኃይሌ ተገደለ፤ መንግሥተ አብ ባህሩ ታሠረ፤ አመሃ አበበ ህቡዕ ገባ፤ ቁምላቸው ተካ በመንግሥቱ ኃ/ማርያም ትእዛዝ ዩጎዝላቪያ ለትምህርት ተላከ።
መንግሥቱ ኃ/ማርያም ከሟሂታቸው ላይ በኢሕአፓ ጥይት የተመቱ ዕለት ማታ ከስብሰባ ወጥተው ጉዞ መጀመራቸውን ለገዳይ ቡድኑ በስልክ የነገረው አመሃ አበበ ነው ተብሏል" ይላል።

**አስተያየት**

ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ ስለነሻምበል አመሃ አበበ ሊገልጹ የፈለጉት-

- ሻምበል አመሃ አበበ የኢሕአፓ አባላ እንደነበር
- አራት ሆነው ስለሻለቃ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ስልጣን መቀረፍ የተወያዩትን ሻምበል ቁምላቸው ተካ ለደርግ ባለሥልጣኖች ሪፖርት ያደረጉ ለመሆኑ ለመግለጽ የሞከሩ ይመስላል።

በእርግጥ ከላይ ስማችሁ የተገለጸው መኮንኖች የአንድ ኮርስ መኮንኖች መሆናችሁን በወቅቱ ሻምበል ቁምላቸው ተካና ሻምበል አመሀ አበበ አንድ ቤት ውስጥ ተከራይተው ይኖሩ እንደነበር ይነገራል።

ከላይ ስማቸው የተገለጸው መኮንኖች ስለሻለቃ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ሥልጣን መቀረፍ ከተወያዩ ከ 15 ቀን በኋላ መቶ አለቃ አለማየሁ ኃይሌ ከተገደሉ ፤ ሻምበል መንግሥተ አብ ባሀሩ ከታሠሩ፤ ሻምበል ቁምላቸው ተካ ከ15 ቀን በኋላ በሻለቃ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ትእዛዝ ዩጎዝላቪያ ለትምህርት ከተላኩ የሻምበል ተስፋዬ ርስቴ እጣ ፋንታ ምን እንደሆነ ሊታወቅ ወይም ሊገለጽ የሚገባው ነበር። ነገር ግን ሊገልጹት ያልፈለጉ ይመስላል። በመሠረቱ አራት ሆናችሁ የተወያያችሁበት እርስዎ ሊጠየቁበት የሚገባ አይመስልዎትም?

እርስዎ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ በወቅቱ እንዳልታሠሩ ይታወቃል። ስለዚህ ሚናዎ ምን እንደነበር አንባቢ ለመገመት አያዳግተውም። እውነቶች በሽፍንፍን ሲታለፉ በተለይም እነሻምበል አመሃና እርስዎም ባሉበት የተወያያችሁትን ጠቋሚው ሟች ሻምበል ቁምላቸው ተካ ብቻ እንደሆኑ አድበስብሰው ለማለፍ መሞከር አግባብና ትክክል ስላልመሰለኝ እውነቱን እንደሚከተለው ለመግለጽ እሞክራለሁ።

ሻምበል በኋላም ኮሎኔል ቁምላቸው ተካን የሟች ወቃሽ አያድርገኝና አራት ሆናችሁ የተወያያችሁበትን በወቅቱ ሻምበል የነበሩት ቁምላቸው ተካ የቅርብ አለቃቸው ለነበሩት ኮሎኔል ረፖርት ያደርጋሉ (ሹክ ይላሉ). በመቀጠልም እርስዎ ሻምበል ተስፋዬ ርስቴም ውይይታችሁ ምን ይመስል እንደነበር ለኮሎኔሉ ያረጋግጣሉ። ኮሎኔሉም ከሻምበል ቁምላቸው ተካና ከእርስዎ የተቸራቸውን ኢንፎርሜሽን ለአንድ የደርግ አባል ሪፖርት ያደርጋሉ። ጥር 26 ቀን 1969 ዓ.ም. የመንፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ሊያካሂዱ የነበሩ ጄኔራል ተፈሪ በንቲ ጨምሮ የደርግ አባሎች ለምሳ ያሰቡንን ቁርስ አደረግናቸው በሚል በሻለቃ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ትዕዛዝ የሞት ቅጣት ይወሰድባቸዋል። ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት በመጀመሪያ ከእርሶና ከሻምበል ቁምላቸው ተካ ያገኙትን ኢንፎርሜሽን ለደርግ ባለሥልጣን ሹክ ብለው የነበሩት ኮሎኔል ወዲያው ወደ ሲቪል የመንግሥት መ/ቤት ምክትል ሚኒስትርነት ይሾማሉ። እርስዎም እንደገለጹት ሻምበል ቁምላቸው ተካ ለትምህርት ወደ ቀድሞው ዩጎዝላቪያ ሲላኩ በተከታታይ ወቅት እርስዎም ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ ለከፍተኛ የመረጃ ትምህርት ወደ ቀድሞ ሶቪየት ሕብረት እንዲሄዱ ያደርጋል። ከሶቪየት ሕብረት እንደተመለሱ ከፖሊስ ሠራዊት ወደ አገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት ተዛውረው ማዕከላዊ ምርመራ ድርጅት ውስጥ ይሠሩ እንደነበር ከእርስዎ ጋር አብረን እንሠራ የነበርነው ቀርቶ በወቅቱ ፖሊስ ሠራዊት ጠቅላይ  መምሪያና አዲስ አበባ ፖሊስ ውስጥ ይሠሩ የነበሩ የፖሊስ አባሎች ያወቁት የነበረ ገሀድ መሆኑን የዘነጉት ይመስለኛል።

በዚህ አጋጣሚ የእኔን ጽሁፍ ለማንበብ እድል የገጠማችሁና ሚስጥሩን ከእኔ በተሻለና በተብራራ መልኩ ለመግለጽ የምትችሉ ብዙ የፖሊስ ሠራዊት አባሎች የነበራችሁ መሆናችሁ ስለሚታወቅ፤

- በሀሰት ፀረ ደርግ አቋም አላቸው በሚል በደርግ የተጨፈጨፉ፣ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው የሠራዊቱ አባሎች የነበሩ ማንነታቸውን፤
- በሀሰት ጥቆማ ለብዙ የፖሊስ አባሎች መሞት፤ እስራትና ስደት ምክንያት የነበሩት ሻምበል ቁምላቸው ተካና ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ ብቻ ሳይሆኑ ብዙ መሰሎቻቸው ስለአሉ ይህ የሚስጥር መጋረጃ በመከፈቱ ማንነታቸውንና ተግባራቸውን ማለት በነማን ላይ ጠቁመው እንዳስያዙና መሰል መረጃዎችን እንድትጽፉና የኢትዮጵያ ሕዝብ በይፋ እንዲያውቀው እንድታደርጉ አለአግባብ ሕይወታቸው ባለፈውና አካለ ስንኩሎች ሆነው በሕይወት በሚገኙ የሠራዊቱ አባሎች በነበሩት ስም እማፀናለሁ።

ስለ አገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር መ/ቤት ቅድሚያ ሠጥቼ አስተያየቴን ልጽፍ የፈለኩት በመዋቅሩ ውስጥ አገለግል ስለነበር ግንዛቤ አለኝ በማለት ሲሆን ስለ መከላከያ ሠራዊታችን የጠለቀ እውቀት ባይኖረኝም ሻምበል ተስፋዬ ርስቴ ስለመከላከያ ሠራዊታችን የፃፉትን መሠረት በማድረግ ያለኝን አስተያየት በማከታተል እንደማቀርብ ቃል እገባለሁ። ቸር ይግጠመን

ሻምበል አስተዋይ